03

3ኛ ዓመት ቁጥር 20
3rd Year No. 20

ባሕር ዳር ሰኔ 21 ቀን 1989ዓ.ም.
Bahir Dar 28th JUNE 1997

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P. O. BOX

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር 20/1989
የአማራ ብሔራዊ ክልል የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ገጽ 12

CONTENTS

Proclamation No 20/1997
A proclamation to provide for the Establishment of Kebele Social Court of the Amhara National Region

Page 12

አዋጅ ቁጥር 20/1989 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልል የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በከተማና በገጠር የቀበሌ መስተዳድር ክልል ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ የራሱን ማህበራዊ ፍ/ቤቶች በማቋቋም በመረጣቸው ዳኞች አማካይነት የራሱን ጉዳይ በራሱ እንዲዳኝ ማድረጉ ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ፣

በዚህ ረገድ ሕዝቡ በየመኖሪያ ቀበሌው የሚያቋቁማቸው የማህበራዊ ፍ/ቤቶች በወንጀልና በፍትሐብሄር ጉዳዩች ላይ ያላቸውን የሥረ ነገር ስልጣን የሚመሩበትም የዳኝነት ሥነሥርዓት በግልጽ መደንገጉ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት በክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 እና 92 መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

Proclamation No 20/1997
A proclamation to provide for the Establishment of Kebele Social Courts of the Amhara National Region

Where as realizing the benifit that people living in urban and rural Kebele adminstration region, using their democratic right, establish their own scial courts inorder to be adjudicated by their nominee judges;

Where as it has become neccessary to clearely stipulate the jurisdiction of social courts to be estabilished by the people in their respective Kebele residences, with requered to criminal and civil matters as well as court procedures;

Now therefore, council of the Amhara National Regional State persuant to sub Article 3/1 of Article 49 and Article 92 of the constitution of the region, here by preclaimed as follows.

164

~~164~~ ~~180~~ 164

ክፍል አንድ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልል የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 20/1989 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. መቋቋም

በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 86/1 ሐ/እና 89/7 በእያንዳንዱ ከተማ እና የገጠር ቀበሌ መስተዳድሩ አንድ አካል ሆነው የሚሠሩ የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል።

3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. "ሕገ መንግሥት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት ነው።
2. " ፍ/ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 መሠረት የተቋቋመውና ከዚህ በኋላ " ማህበራዊ ፍ/ቤት" እየተባለ የሚጠራውን አካል ነው።
3. "ዳኞች" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚቋቋሙት የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ተግባራት እንዲያከናውኑ የሚመረጡትን ዳኞች ነው፣
4. " የወረዳ ፍ/ቤት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 11/1988 ዓ.ም አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመውን የበታች ፍ/ቤት ነው።

4. አላማዎች

የማህበራዊ ፍ/ቤቶች የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፣

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክና በአማራ ብሄራዊ ክልል ሕገ መንግስት የተረጋገጡትን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ጥቅሞችን ማስከበር፣
2. በተቋቋመባቸው ቀበሌዎች ውስጥ ባሉ ነዋሪዎች መካከል መግባባት ፣ አብሮ በሰላም መኖር እንዲሰፍን መጣር ፣
3. ነዋሪዎች የሕግን የበላይነት ተገንዝበው ሕግን ማክበር አኩሪ ባሕላቸው እንዲያደርጉትና እንዲሁም በፍትህ ሥራ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሕግ እውቀታቸውን ማዳበር።

PART ONE

1. Short Title

This proclamation may be cited as "A Kebele Scial Courts of the Amhara National Regional Establishing proclamation No 20/1997."

2. Establishiment

In accordance with Aticle 86/1/c and Article 87/7 of the constitution of the Amhara National Regional Kebele Social Courts are here by established by this proclamation in each respective urban and rural kebeles, that function as the part of the administration of the same.

3. Definition

Unless the context requires otherwise in this proclamation

1. "Constitution" means the constitution of the Amhara National Regional
2. "Court" means a body established, persuant to Artcle 2 of this proclamation and here in after refered to as Scial curt.
3. "Judges" means judges nominated to adjudicate cases in the Kebele Social Courts to be established persuant to this proclamation
4. "Woreda Court" means a lower court established in accordance with article 3 of the of Amhara National Regional State Court establishement proclamation NO 11/1988.

4. Objectives

The social courts shall have the following objectives

1. Realize the human democratic rights and benifits ensured under the constitutions of the Ethiopian Federal Democratic Republic and the Amhara National Regional State,
2. Make efforts to maintain peace and good neighbourly relation among residents of kebele where they are established,
3. Raise the residents legal awearness inorder that they may understand the concept of the rule of law, and make respect for the law their proud culture as well as enabling them participate in juicial functions,

ክፍል ሁለት
ስለ ዳኝነት ሥራ አካሄድ

5. ስለ ዳኝነት ነጻነት

የማህበራዊ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ ፣ ከህግ በቀር በሌላ ሥልጣን አይመሩም።

6. በግልጽ ችሎት ስለማስቻል

1. ማህበራዊ ፍ/ቤት ማናቸውንም ጉዳይ የሚያየው በግልጽ ችሎት ይሆናል ፣ ሆኖም ለህዝብ መልካም ፀባይ ወይም ዳኝነት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዝግ ችሎት ያስችላል።
2. ማህበራዊ ፍ/ቤት በተበሌው መደበኛ ችሎት ሥፍራ ያስችላል ፣ ሆኖም ለትምህርታዊነቱና ለቀልጣፋ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በተበሌው ውስጥ በሌላ በማናቸውም ስፍራ ያስችላል።
3. እያንዳንዱ ማህበራዊ ፍ/ቤት የሕዝቡን የሥራ ፣ የኑሮና የእምነት ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የማስቻያ ቀንና ሰዓቱን ይወስናል።

7. ከችሎት ስለመነሳት

1. ማንኛውም የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ ተከራካሪ ወገኖች ከአንደኛው ጋር የቅርብ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ወይም ከተከራካሪ ወገኖች ከአንደኛው ጋር ፀብ ያለው ወይም ከርክሩ የተነሳበት ነገር አስቀድሞ በዳኝነት በእርቅ መንገድ ያየው ከሆነ ከዳኝነት ይነሳል።
2. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መኖራቸውን ያውቀ የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ በራሱ ፍቃድ ከችሎቱ መነሣት አለበት።
3. የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ በራሱ ፍቃድ ካልተነሳ ከተከራካሪዎች ተቃውሞ ሊቀርብበት ይችላል ፣ ሌሎች የፍ/ቤት ዳኞችም ተቃውሞውን መርምረው አባሉ ከችሎት ስለመነሣቱ ወይም ስለ አለመነሣቱ ውሣኔ ይሰጣሉ።
4. የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ ከችሎት ይነሣል፣ ወይም አይነሣም ተብሎ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም።
5. አንድ ዳኛ ከችሎት ሲነሣ በተጠባባቂው የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ ተቋውሞ የቀረበበትን ጉዳይ ተክቶ ይሰማል።

PART TWO
Judicial Function

5. Judical Independence

The judges of the social courts shall excercise their judicial function in complete independence; they shall be guided by other authority than that of all law

6. Hearing in Public

1. The social courts hear cases in public, provided, however, that where public morality and safety, so require the hearing shall incamera.
2. The social court shall held hearings at its normal place of sitting in the Kebele. However, it may hold hearings at any other place with in the kebele where it finds it nesessary for educatinal value and the prompote discharge of judical function.
3. Each social court shall determine the holding day and time of its hearing taking into account condition of occupation, life style and faith of the people.

7. Withdrawal of Judges

1. A judge of social court may not sit in procedings of a case where he has close consaqunit or affinity or personal conflict with one of the partics or previously has been involved in the case as a judje or consulator.
2. A judge of a social court who realized the existance of the condition, innumirated under sub Article 1 of this article shall withdraw from the case.
3. Objection may be loged by the parties, where the judge of the social court does not with draw from the case on his own will. The other judges of the court decided by examining the challenge whether or not the judge should be withdrawn from the case.
4. No appeal shall be loged upon the decision whether or not a judge of a social curt should be withdrawn from the case.
5. The reserve judges of the social court shall replace and hear the case where a judge is withdrawn from the case.

ክፍል ሶስት

8. የዳኞች ምርጫ

1. የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞች በቀበሌው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅራቢነት በቀበሌው ም/ቤት ይሾማል።
2. የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት አባል ሆነው የሚመረጡ ዳኞች መልካም ስነ ምግባር ያለው/ ያላት መሆን ይኖርበታል/ ይኖርባታል።

9. የአገልግሎት ዘመን

1. የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ የአገልግሎት ዘመን የቀበሌው መስተዳድር የአገልግሎት ዘመን ይሆናል።
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም፣ የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ ሆኖ የተመረጠ ሰው በማንኛውም ጊዜ ቀበሌውን ለቆ ሲሄድ የአገልግሎቱ ዘመን የሚቋረጥ ይሆናል።

10. የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛን ከዳኝነት ሥራ ስለማንሣት

1. ማንኛውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ የተመረጠበትን ሃላፊነት በሚገባ ሣይወጣ የቀረ እንደሆነ ወይም የሥነ ምግባር ጉድለት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ በቀበሌው ም/ቤት ከሥልጣን እስከ መነሣት ድረስ ተገቢው እርምጃ ይወሰድበታል።
2. የቀበሌው ም/ቤት ስብሰባ እስከሚካሄድ ድረስ በፍትሕ ሥራ ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የቀበሌው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሥነ ምግባር ጉድለት የፈጸመውን የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኛ ከዳኝነት ሥራው አግዶ ሊያቆየው ይችላል።

11. ስለዳኞች ብዛት

በማንኛውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች እንዲሁም ዳኛ ሲጓደል ተክተው የሚሠሩ ሁለት ተጠባባቂ ዳኞች ይመረጣሉ።

12. ስለችሎት ማሟላት

የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት አንዱን ጉዳይ የሚያየው ሶስት ዳኞች በሚገኙበት ችሎት ይሆናል።

PART THREE

8. Electorol of judges.

1. Judges of the social court being presented by the execution committe of the kebele shall be appointed by the counted of the same.
2. The persons to be elected as judges of the social courts shall have good manner.

9. Term of office.

1. The term of the judges of the social court shall be the term office of the administration of the Kebele.
2. Despite the above mentioned sub Article 1, the term of adjudge of the social court shall terminate where he changes his place of residence from his kebele.

10. Removal of judges of kebele social courts.

1. A judge of the social court may at any time be removed from office by the council of the kebele. due to failure to properly discharge his duties when found committed in moral action.
2. Until the council of the kebele hold meetings, to avoid risks in the justices work, the executive committee of the kebele shall remove the judge of the social court who committed immoral action.

11. Numbers of judges.

In every kebele social court there shall be priding judge end two other judges as well as two alternate judges.

12. Constitution of chelot.

The social court shall have a chalot composed of three judges to hear the case.

ክፍል አራት

ስለቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን

13. ስለ አስተዳደር ክልል ስልጣን

1. ማንኛውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ አንዱን ጉዳይ የማየት የአስተዳደር ክልል ሥልጣን የሚኖረው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንዱ የተሟላ እንደሆነ ነው፥
   1.1 ተከሣሹ የሚኖረው ፍ/ቤቱ በተቋቋመበት ቀበሌ ውስጥ ሲሆን
   1.2 ክርክር ያስነሣው ጉዳይ የሚገኘው ወይም የተፈጸመው ፍ/ቤቱ በተቋቋመበት ቀበሌ ውስጥ ሲሆን
   1.3 ጥፋቱ የተፈጸመው ፍ/ቤቱ በተቋቋመበት ቀበሌ ውስጥ ሲሆን

2. አንዱ ክስ ከአንዱ በላይ ፍ/ቤቶች የቀረበ እንደሆነ የክሱ ማመልከቻ በቀደምትነት የቀረበለት ማህበራዊ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ተቆጥሮ ውሣኔ ይሰጣል፥

14. የፍትሐብሔር ጉዳዬች ሥረ ነገር ሥልጣን

1. ማንኛውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት፥

   1.1. ከብር 1000.00 (ከአንድ ሽህ ብር) የማይበልጥ የገንዘብ ወይም ግምቱ ከብር 1000.00 (ከአንድ ሽህ ብር) የማይበልጥ ማናቸውም የንብረት ክርክር
   1.2. በገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ ስለሚነሱ የመሬት ይዞታ ክርክሮች
   1.3. በገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኙ ቤቶችንና ቦታዎችን የኪራይና የአገልግሎት ክፍያዎች በመጠየቅ የሚነሱ ክርክሮች
   1.4. በከተማ የቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኙ ቤቶችና ቦታዎች በተመለከተ ከብር 500 የማይበልጡ የኪራይና የአገልግሎት ክፍያዎችን በመጠየቅ የሚነሱ ክርክሮች፥

   * 1.5. በፍትሐብሔር ህግ ስለ ቅርንጫፎችና ስለ ዛፎች (1222) አጥር ወይም ቤት ስለማደስ (1218) ስለ ጠፉ ነገሮች ወይም እንሰሶች (1219) ስለመተላለፊያ ቦዬችና ቧንቧዎች (1220) ስለ መተላለፍ መብት (1221) ስለ ዝናም ውኃ (1243) እና ከወደታች ስለሚገኙ መሬት ግዴታዎች (1246) የሚነሱ ክርክሮች

PART FOUR

Jurisdiction of kebele social courts.

13. Local jurisdiction.

1. The kebele social court shall have local jurisdiction to hear a case only when one of the following situations gets fulfilled:-

   1.1 The accused resides,

   1.2 The subject matter of the dispute is located or committed wherethe social court established.
   1.3 The offense is committed with in the kebele of its establishment.

2. Where the case is submitted to more than one court, the court to which submission is first made shall be deemed to have jurisdiction and shall decide the case.

14. Material jurisdiction concerning civil cases.

1. The kebele social court shall have the power to hear and decide the following:

   1.1. Any dispute involving pecuniary claims not exceeding birr 1000 (one thousand) or property claims having an estimated value no exceeding birr 1000 (one thousand).
   1.2. Dispute involving claims of land possessions with in the rural kebeles regions.
   1.3. Dispute involving claims of houses , lands, rents and service charges with in the regions of the rural kebeles.
   1.4. Dispute involving claims of rent and service charges not exceeding birr 500 (five hundred), renting to houses and lands with in the boundary of urban kebele.

   1.5. Claims beside on the civil code regarding branches and roots (Art 1212),repair of wall or building (Art 1218),lost things (Art 1219),installation of pipes (Art 1220),right of way (Art 1221), rain water (Art 1245), and duties of land owners below (Art 1246)

168

1688 ± 1687

1.6. በኅጠር ቀበሌ መስተዳድር ወይም በሕብረት ሥራ ማህበራት ክልል ውስጥ የጋራ መጠቀሚያ በሆኑ ሥፍራዎችና በአገልግሎት ዋጋ ክፍያ ምክንያቶች በማህበሩ አማካኝነት ለሰሚሰጠው ብድር አክፋይ በማህበሩና በአባሉች መካከል የሚነሳውን ማናቸውም ክርክር የማየት ስልጣን ይኖረዋል።

2. ማንኛውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት በመንግስት አካላት ለሚሰጥ ነፃ አገልግሎት የአመልካቹን የኑሮ ሁኔታ አረጋግጦ ማስረጃ ይሰጣል።

15. የወንጀል ጉዳዬች የስረ ነገር ስልጣን

ማንኛውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት

1. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ ከ734-737፣ ከ745-757፣ ከ760-764፣ከ768-775፣ ከ777-782፣ ከ784-785፣792-816፣ ሥር የሚነሱ የደንብ መተላለፍ ክሶችን በመጀመሪያ ጀረጃ አይቶ የመወሰን

2. የወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ለቀበሌ መስተዳደር የሚመራቸውን ሌሎች የደንብ መተላለፍ ክሶች በመጀመሪያ ጀረጃ አይቶ የመወሰን ስልጣን ይኖረዋል።

16. ሰለቅጣት

ማንኛውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት

1. ተከሣሹ ጥፋተኛ መሆኑ በሚገባ ሲረጋገጥ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቅጣቶች መካከል እንደ ጥፋቱ ክብደት በአንዱ ሊቀጣው ይችላል።

1.1. ማስጠንቀቂያ ወይም

1.2. ጥፋተኛው ተበዳዩን ሰው ይቅርታ እንዲጠይቀው ማድረግ ወይም

1.3. እንደተከሳሹ የመክፈል አቅም በአንድ ወይም በየጊዜው ተከፍሎ የሚያልቅ ከብር 1 እስከ 300 የሚደርስ የገንዘብ መቀጫ መቅጣት ወይም

1.4. ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ ከአስራ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ የህብረተሰቡን ጠቃሚ የሆነ ከሙያው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሥራ ማሠራት ወይም

1.5. እስከ አንድ ወር ሊደርስ የሚችል እስራት መቅጣት ወይም

1.6. ጥፋቱ የተፈፀመው በሕብረት ወይም በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ ከሆነ በክሳሽ ጠያቂነት ከብር 500 ያልበለጠ ካሣ ማስከፈል።

2. ተደጋጋሚ ወይም ከአንድ በላይ ጥፋቶች ፈፅሞ በተገኘ ተከሳሹ ላይ ማህበራዊ

1.6 Dispute arising between peasant associations or agricultural producers co operates and their members concerning fees for the collective use of lands and instruments or payments of loans advanced through the peasant association or the cooperative.

2. The Social court may examine and acrtity the means of livelihood of an applicant for free services rendered by goverement organs.

15. Material jurisdiction concerning criminal cases.

Any social court shall have the power to hear and decide in first instances.

1. Offenses under from article 734-737, 745 ,757, 760-764, 768-775, 777-782, 784-785 and 792 -816.

2. Any offenses under the code of petty offenses when regress to it by the woreda justiee office.

16. Penalties.

1. Where the accused is proved to be guilty beyond reasonable doubt the court may impose ,according to the gravity of the offense ,any one of the following penalties.

1.1. Warn the offender, or

1.2. Order the offender to make an appology to the injured person, or

1.3. Impose fines of up to birr 300(three hundred) to be paid immediately or with in a fixed period of time ,or

1.4. Impose for on period of not exceeding 15 (fifteen) days ,a sentence of compulsory labour which is related to the trade of the offender and useful to the community to be carried outside the regular working hours, or.

1.5. Impose a sentence of confinement not exceeding one month, or

1.6. Order, when the offense has caused bodily harm or damage to property, the payment of compensation not exceeding birr 500 (five hundred) when the injured party so claims.

2. The social court may impose more than one penalties prescribed under sub Article one

ፍ/ቤቱ ክሳይ በንዑስ አንቀጽ 1 ከተመለከቱት ከአንድ በላይ የሆኑ ቅጣቶችን መወሰን ይችላል።

3. አስፈላጊ መሆኑን ካመነበት የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት በንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ከተዘረዘሩት ቅጣቶች በተጨማሪ ተከሳሹ የደምብ መተላለፍ ጥፋት የፈፀመበት መሣሪያ በውርስ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ለማዘዝ ይችላል።

4. ተከሣሹ ጥፋቱን የፈፀመው በሕዝብ መዝናኛ ሥፍራዎች፣ በመጠጥ ቤቶች ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ስፍራዎች ከሆነ የፍርድ ኮሚቴው ካመነበት ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ እንዳይገኝ በማድረግ ተጨማሪ ቅጣት ሊወስንበት ይችላል።

5. ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ቅጣቱንየሚወስነው የጥፋቱንክብደት፣ ያጥፊውን የኑሮ ሁኔታ፣ የገቢውን መጠንና ሰለቤተሰቡ አስተዳደር ያለበትን ኃላፊነት በማመዛዘን ይሆናል።

17. ችሎት ስለመድፈር

1. ማንኛውም በማህበራዊ ፍ/ቤት በችሎት ላይ አንዳለ የስድብ፣ የዛቻ፣ የፈዝ ወይም ሌላ ተመሣሣይ የሁከት ድርጊት የፈፀመንሰው ቀጠሮ ሳያደርግ ወዲያውኑ ዝርዝር ሁኔታውን በመመዝገብ ከብር 100 (አንድ መቶ) በማይበልጥ መቀጫ ሊቀጣው ይችላል።

2. በችሎት ወይም ከችሎት ውጭ የኃይል ድርጊት ለመፈፀም በመጋበዝና የፍርድ ቤቱን ሥራ በማሰናከል ሁከት የፈጠረን ሰው ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ከአስር ቀን ባልበለጠ የእስራት ቅጣት ሊቀጣው ይችላል።

ክፍል አምስት
የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የዳኝነት ሥነሥርዓት

18. መሠረቱ

1. የማንኛውም ማህበራዊ ፍ/ቤት የሚከተለው የዳኝነት ሥነ ሥርዓት በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

2. ማንኛውም ሰው በችሎት በመገኘት በቀረበ ጉዳይ ላይ የችሎቱን ስብሰባ አስፈቅዶ ትችት የማቅረብ መብት ይኖረዋል፣ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጠው ህግን ብቻ ተከትሎ ይሆናል።

19. ስለክስ አመሰራረት

1. ለቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የሚቀርብ ክስ እንደ ጉዳዩ ክብደት በጽሁፍ ወይም በቃል ሊሆንይችላል።

2. ክሱ በፅሁፍ በሚሆንበት ጊዜ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፣ ክሱ በቃል በሚቀርብበት ጊዜ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ መዝገብ ቤት በመክፈት የከሳሽና

here of, where the accused is a habitual offender or found guilty of more than one offenses.

3. The social court may, where it deems it necessary ,in addition to penalties prescribed under sub-Article two hereof, order the confiscation of the instrument with which the petty offense is committed.

4. The social court may, where it deems it necessary, order an additional measure prohibiting the ,accused , for period not exceeding one month, from going to public recreationotters, bars or such other similar places where the offense no committed.

5. In assessing sentence the social court shall take into account the gravity of the offense, the personal circumstances, the level of income and the family responsibility of the caused.

17. Contempt of chelot.

1. The social court may summarily punish with fine not exceeding birr 100 (hundred) any person who ,in the course of its proceedings, obstructs its hearings with insults, intimidation , ridicule or other similar acts of disturbance.

2. The social court may sentence a person to imprisonment not exceeding ten days where he is out side or inside the court , aggitated to committee an out of violence and create a disturbance on the preceeding of the court.

PART FIVE
Procedures of kebele social courts

18. Principle.

1. Any social court shall follow the procedures provided for in this proclamation.

2. Any person may , up on permission by presiding judge, forward his views and opinions on the case under consideration , provided however, that the decision of the court shall be beside on law.

19. Institution of proceedings.

1. A case, instituted before a social court , may, according to the gravity of the case, be presented in writing to orally or,

2. When in writing , it shall be prepared in two copies when presented orally, the court shall prepare a file where in the names and addresses of the parties as well as the

የተከሳሽን ስምና አድራሻ እንደሁም የክሱን ፍሬ ነገር በአጭሩ የቀረቡትን ማስረጃዎችና ምስክሮች በጽሁፍ ያሰፍራል።

3. የማህበራዊ ፍ/ቤት ሰብሳቢ ለፍ/ቤቱ የሚቀርቡትን ማመልከቻዎች በመመርመር አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችና ማስረጃዎች ለኮሚቴው ተያይዘው እንደቀርቡ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፣ እንደሁም በኮሚቴው ትዕዛዝ ተከራካሪ ወገኖች፣ ምስክሮችና ሌሎች ጉዳዩን ለማጣራት አስፈላጊ የሆኑ ሰዎች መጥሪያ እንደደርሳቸው ያደርጋል።

20. ስለ ክስ አቀራረብ

ለማህበራዊ ፍ/ቤት የሚቀርቡትን የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች በሚመለከት ክሱ የሚቀርበው በሚከተለው አካኃን ነው፣

1. የደንብ መተላለፍ ጥፋት የተፈፀመው በሰው አካል፣ ነፃነት፣ ክብር ወይም ንብረት ላይ ሲሆን ክሱን ማቅረብ የሚችለው ተበዳይ እራሱ ወይም ህጋዊ ወኪሉን (ነባረ ፈጅ) ብቻ ነው፣
2. የደንብ መተላለፍ ጥፋት የተፈፀሙት በክልሉ መንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም ላይ ከሆነ ግን ክሱ የሚቀርበው በሚመለከተው የቀበሌ ጽ/ቤት አማካኝነት ይሆናል።

21. ስለ መጥሪያ አሰጣጥ

1. በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ተከሶ የሚቀርበው ማንኛውም ሰው የተከሰሰበትን ጉዳይ አስቀድሞ እንደያውቀው ተዘጋጅቶ እንደቀርብ ጉዳዬ የሚሰማበትን ቀን ሰዓትና ስፍራ የከሣሽ ስምና የክሱ ዓይነት በአጭሩ ተገልጾ መጥሪያ ይላክለታል።

2. ከቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ለተከራካሪ ወገኖች ወይም ለሚፈለጉ ሌሎች ሰዎች የሚተላለፈው መጥሪያ በጽሁፍ ይሆናል።

22. ማስረጃ እንዲቀርብ ስለመጠየቅ

1. ማንኛውም ማህበራዊ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ለመወሰን የሚያስፈልጉትን ምስክሮች ለመጥራትና የጽሁፍ ማስረጃዎች አስቀርቦ ለማየት ይችላል።
2. ማንኛውም ሰው ወይም መ/ቤት ወይም ድርጅት የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ሲጠራው መቅረብ ወይም የተጠየቀውን ማስረጃ በተገቢው ጊዜ ውስጥ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

summary facts of the case, the list of the evidence and witnesses shall be entered.

3. The presiding judge of the social court shall examine the application and make the necessary preparation to ensure that the necessary documents and evidences are submitted. The presiding judge shall issue summons to the parties, witnesses and other persons required to give evidence.

20. Prosecution

The proceedings of petty offenses falling under the jurisdiction of the social courts shall be as follows.

1. Offenses relating to bodily injury, freedom honor and property shall be instituted by the victim himself or his representative.

2. Offenses committed against the benefit of the regional state and the people shall be instituted by the concerned kebele office.

21. Serving of summons.

1. Any person against whom proceedings are instituted before the kebele social court offered advance notice of the case against him to prepare his defense and notice of the case against him to prepare his defense and appear before the court by serving him the date, time and with a summons in which place of hearing; as well as the name of the plaintiff and a summary of the case of action shall be specified.
2. Summons issued to the parties or other persons required to appear before the court shall, as foresee possible, be in writing.

22. Production of evidence.

1. Any social court may require the attendance of any witness or the production evidences necessary for the decision of the case.

2. Any person or office or organization shall have the duty, upon notice by the court, to appear before it or to produce evidence with in the proper time.

23. ጥሪ ስለማከበር

1. በደንብ መተላለፍ ጉዳይ አንዱ ተከሳሽ በችሎት እንዲገኝ መጥሪያ ደርሶት፣ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነየሚቀጥለው ቀንቀጠሮ ተገልጾ ተጨማሪ መጥሪያ ይተላለፍለታል፡፡ ሁለተኛ ጥሪ ያላከበረ ተከሳሽ በሶስተኛ ቀጠሮ በክፍሉ ፖሊስ ወይም በፀጥታ ኮሚቴ አማካኝነት እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

2. ማህበራዊ ፍ/ቤቱ የቀረበው ጉዳይ የፍትሐብሔር ክርክርን የሚመለከት ሲሆንእና ከሣሹ በቀነ ቀጠሮው ሣይቀርብ ቢቀር ቀርቦ ለመከራከር አንድ ተጨማሪ እድል ይሰጠዋል፣ በሁለተኛው ቀነ ቀጠሮ ሣይቀርብ ቢቀር ግን ፍ/ቤቱ ከሣሽ ክሱን እንደተወው ተቆጥሮ የክሱን መዝገብ ይዘጋል፡፡

3. በፍትሐብሔር ጉዳይ ተከሣሽ ሣይቀርብ ቢቀር ለሁለተኛ ጊዜ መጥሪያ እንደደርሰው ያደርጋል፣ ጥሪውን ሣያከብር የቀረ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተከሣሽ በሌለበት ጉዳዩ አይቶ ሊወስን ይችላል፡፡

24. የተዘጋን መዝገብ እንደገና ስለመክፈት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 ወይም ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በሁለት ቀኑ ቀጠሮ ሣይቀርብ የቀረ ከሣሽ ወይም ተከሣሽ የቀረው አክል ስላጋጠመው ከሆነ ምክንያቶቹን በማመልከቻ በዝርዝር በመግለፅ እንደነገሩ ሁኔታ የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈት ወይም የተሰጠው ውሳኔ እንደገና እንዲታይ ለማህበራዊ ፍ/ቤቱ ሊያመለክት ይችላል፡፡

2. ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ከሣሽ ወይም ተከሣሽ ሣይቀርብ የቀረው በበቂ አክል ምክንያት መሆኑን ሲረዳው በአንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከሣሹ ባለመቅረቡ ምክንያት የተዘጋውን መዝገብ እንደገና ከፍቶ ለመመርመር ወይም በአንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠው ውሣኔ ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለማድረግ ይችላል፡፡

3. የተዘጋ መዝገብ በበቂ ምክንያት እንዲከፈት ወይም የተሰጠው ውሣኔ በበቂ ምክንያት እንደነሣ የሚቀርብ ማመልከቻ አክሉ ቢተወገደ በ15 ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረበ ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል፡፡

25. እንደ በቂ አክል የሚቆጠሩ ሁኔታዎች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 (3) መሠረት በቂ አክል ተብለው የሚቆጠሩ ከአልጋ ለመነሣት የማያስችል ህመም፣ የቅርብ ዘመድ ሞት፣ ወይም ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር

23. Failure to appear

1. Where , in the case of petty offense, a defendant fails to appear as summoned before the court , a second summons shall be served notifying him of the date of thinnest hearing . where he fails to comply with the second summons, the court shall issue a bench warrant for his appearance through the police unit or defense squad of the kebele.

2. Where, in the case of a civil dispute, the plaintift fails to appear on the day of hearing, he shall be given one other chance. where he fails to oppear for the second time , the court shall dismiss the case unless it pending for decision.

3. Where, in the case of a civil dispute, the defendant faills to appear before the social court, a second summon shall be served on him. where he fails to appear for the second time, the case shall be heard expartie.

24. Reopening

1. Plaintiff or defendant, who for good cause fails to appear for the second time as provided in sub-Articles (2) or (3) of Article 23 hereof, may apply to the court state his reasons in detail , to reopen the case or to rexamine its decision as the case may be.

2. Where the court is satjsfied that plaintiff the defendant failed to appear before it for good case, it may reopen the case closed pursuant to Article 23(2) for failure of the plainfift to appear, or to reexamine its decision given exparte pursuant to Article 23 (3) here of

3. Application for the reopening of the cause for good cause, or for re- examining a decision for good case shall be submitted with in 30 (thirty) days from the day the cause ceases to exist . Any application submitted after the expity of this time limit, shall not be entertained.

25. Good cases

For the purpose of Article 24 (3) of this proclamation , bed confining inner, death of a close relative, conditions preventing movement from place to place , or other similar cases of

የማያስችል ወይም ሌሎች ተመሣሣይ ከአቅም በላይ ሁኔታዎች መኖር ናቸው።

26. ስለ ክሱ መሰማት አጀማመር

1. ማህበራዊ ፍ/ቤት ክስ እንደሰማ በቀጠረበት ቀንና ሰዓት ያስችላል
2. ፍርድ ቤቱ ክሱን መሰማት ከመጀመሩ በፊት በመዝገብ ውስጥ የተጠቀሱት ተከራካሪ ወገኖች በችሎት መገኘታቸውን ያረጋግጣል፣
3. ክሱ ደንብ መተላለፍን የሚመለከት ሲሆን፣ ክሱን እንዲሰማና መከላከል እንዲችል ተከሣሽ እራሱ በችሎት መገኘት ይኖርበታል።

27. ክሱን ስለ ማንሣት

ማንኛውም ከሣሽ ማህበራዊ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ፍርድ ወይም ውሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ በማናቸውም ጊዜ ያቀረበውን ክስ ማንሣት ይችላል።

28. ክሱን ስለመዝጋት

ማንኛውም የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የፍትሐብሄርን ጉዳይ ማየት ከጀመረ በኃላ ጉዳዩ ክስልጣኑ በላይ ሆኖ ሲያገኘው ክሱን ዘግቶ ባለጉዳይን ያሰናብታል።

29. ስለ ውሣኔ አሰጣጥ

ማንኛውም ማህበራዊ ፍ/ቤት

1. የሚሠጠው ውሳኔ በተቻለ መጠን ሙሉ ድምፅ ይሆናል፣ ሙሉ ድምፅ ካልተገኘ ውሣኔው በድምፅ ብልጫ ይሰጣል አነስተኛ አስተያየት በውሣኔው ላይ ይመዘገባል።
2. ውሣኔውን በሚሰጥበት ጊዜ በክርክሩ ሂደት ላይ የቀረቡትን ነጥቦችና መረጃዎች በመግለፅ ለውሣኔው መሠረት ያደረጋቸውን ምክንያቶች በአጭሩ በፍርዱ ላይ ያሰፍራል።
3. የቀረበው ክስ ውስብስብነትና ከማስረጃ አቀራረብ ጋር የተያያዙ ችግሮች ካላጋጠሙት በስተቀር ማህበራዊ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ መስጠት ያለበት ክሱ ከቀረበለት ጊዜ አንስቶ እጅግ ቢዘገይ እስከ 45 ቀናት ባሉት ጊዜያቶች ውስጥ መሆን ይኖርበታል።

30. ስለ ይግባኝ

1. ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ ለማቅረብ እንደሚፈልግ ውሳኔው በተሰጠ በአምስት ቀን ውስጥ ለፍ/ቤቱ ያሣውቃል፣ ፍ/ቤቱም የመዝገቡን ትክክለኛ ግልባጭ በ15 ቀን ውስጥ እንደሰጠው ያደርጋል።

force major shall be deemed to be good cause.

26. Proceeding of court hearing.

1. The social court shall sit on the date and time fixed for hearing.
2. The court shall ensure the attendance of the parties before hearing starts.
3. If the case relates to violation of petty offense, the defendant shall appear in person ignored to be able to defend himself

27. With drawal

Any plainfift or accuser may withdraw his case at any time before the social court renders its decision.

28. Dismissal of a case.

Where in the course of proceedings of a civil case, the kebele social court discovers that the case falls outside its jurisdiction, it shall dismiss such a case.

29. Decision making.

The social court shall;

1. As fore as possible , be made by unanimous vote. in the absence of unanimity, the decision shall be made by a majority vote. The dissenting opinion shall also be recorded there with.
2. In its decision , specify in brief the facts of the cease, the evidences produced and the reasons for the decision.
3. The social court shall render its decision with in 45 (forty five) days from the institution of the suet unless and otherwise it is confronted with problems related to complaints and introduction of evidences for the case.

30. Appeal.

1. Any party aggrievated by the decision of the court shall notify the court of his desire to appeal with in 5 (five) days of the pronouncement of the decision. The court shall cause to be given to the appellant a certified copy of the decision with in 15 (fifteen) days from the date of notification.

173

2. ይግባኝ ባይ የመዝገቡ ግልባጭ በደረሰው በ10 ቀን ውስጥ ይግባኙን ለወረዳው ፍ/ቤት ያቀርባል።
3. የወረዳ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።
4. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈጽሞ ሲገኝ ወይም በሥነ ሥርዓት ሕጎች ውስጥ የተመለከቱት ሌሎች ምክንያቶች ተጥሰው የተገኙ እንደሆነ፣ ውሣኔው በከፍተኛ ፍ/ቤት በኩል በስበር ታይቶ ሊስተካከል ይችላል።

2. The appellant shall lodge his appeal to the wereda court with in 10 (ten) days of the receipt of the copy of the decision.
3. The decision of the wereda court shall be final.
4. With out prejudice to sub Article 3 of this article where the wereda court , in its final decision committes fundamental error of law or contradicts the reasons specified by procedural laws, such a decision shall be rectified through the high court by the way cessation.

31. ስለ ውሣኔ አፈፃፀም

1. በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ካልታገደ በስተቀር ውሣኔው ከተሰጠ ከ20 ቀን በኋላ አፈፃጸሙ ይቀጥላል።
2. ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ እራሱ ለማስፈፀም ወይም አግባብ ያለው ሌላ አካል እንዲያስፈፅመው ለመወከል ይችላል።
3. የሚወሰነው መቀጫ ለመንግስት ገቢ ይሆናል።
4. ማንኛውም ሰው የመክፈል ችሎታ ያለው የተወሰነበትን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ውሣኔው በንብረት ላይ እንዲፈፅም ያዝዛል።
5. የተወሰነውን መቀጫ ጥፋተኛው የፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካመነ ቅጣቱን ወደ ማህበራዊ ሥራ ሊለውጥለት ይችላል።
6. በዚህ አዋጅ የማረፊያ ቤት የእስራት ቅጣት በተመለከተ የሚያስፈፅመው፣ የቀበሌ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ በቀበሌ ውስጥ ለማረፊያ ቤት አገልግሎት እንዲውል በሚመድበው ቤት ውስጥ ይሆናል።

31. Execution of discision

1. Unless a stay of execution is ordered by the appellant court the decision of the social court shall be executed 30 (thirty) days offer the pronouncement of decision.
2. The social court may itself execute the decision or delegate another appropriate body to execute same.
3. Fine imposed by the court shall be transferred to the state treasurey.
4. The social court shall order the execution of the decision on the property of person where, although capable, he refuses to pay the fine imposed.
5. Where the social court believes that the person failed to pay the fine due to causes beyond his control , it may convert the fine into compulsory labour.
6. Under this proclamation an ordered confinement shall be executed in such a place, determined by the executive committee of the kebele to be place of confinement with in the kebele.

ክፍል ስድስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART SIX
Miscellaneous provisions.

32. ስለ ወጭ

ለፍ/ቤቱ የሚቀርበው ጉዳይ ላይ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን የራሱን ወጭ ይችላል፣ ሆኖም ከሣሽ ክስ ያቀረበው ሆነ ብሎ ተከሣሽን ለማጉላላት መሆኑን ፍ/ቤቱ ካመነበት ለተከሳሹ እስከ ብር 100 (አንድ መቶ) ብር የደረሰ ኪሳራ ከሳሽ እንዲቀጥበት ሊወሰን ይችላል።

32. Expenses.

Each party to a dispute shall bear his own expenses. If however, the court has reason to believe that the plaintiff instituted the case with the intention of harassing the defendant, it may order the plaintiff to pay up to birr 100 (one hundred) to the defendant by way of damage.

3. ዘገባ ስለማቅረብ

ፍ/ቤቱ ስለ አከናወናቸው ተግባራትና ስላጋጠሙት ችግሮች ለክፍሉ ቀበሌ መስተዳድር አግባብ ላለው የወረዳ ፍ/ቤት

33. Report.

The social court shall, from time to time submit report to the administration of its kebele and to the presiding judge of the concerned

ሰብሳቢ በየጊዜው ዘገባ ያቀርባል።

34. የመተባበር ግዴታ

የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት አባል የሚሠራበት ማንኛውም መ/ቤት ድርጅት ወይም ማህበራዊ ተቋም ግለሰቡ የተመረጠበትን ሕዝባዊ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችል ተገቢው ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለበት።

35 ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

36. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል።

37. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ም/ቤት ፀድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ሰኔ 21 ቀን 1989 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት

woreda court .

34. Duty to cooperate.

Any office , organization, institution or association employing a judge of the social court shall extend the necessary assistance to the judge in the proper caring out of his activities.

35. In applicable laws.

Any law, regulations or directives ,inconsistent with this proclamation shall not apply in respect of matters provided for here in.

36. Power to issue regulation

The regional excutive committee shall have the power to issue regulation and directives for the purpose of implimenting this proclamation.

37. Effective date.

This proclamation shall come in to force on the date of its ratification by the council of the region.

Done at Bahir Dar
This 28th day of June 1997
Council of the Amhara National
Regional State